# ለልጅ ከሳቁለት፣ ለውሻ ከሮጡለት

ጫንያለው ይንበርበሩ

የትም እየሮጬኸ፣ ላንቃውን በመክፈት፣
ይኸ ውሻ አበደ፣ አሁንስ ለየለት።

ወያኔና ውሻ ይመሳሰላሉ፣
የሚፈራቸውን፣ በግምት ያውቃሉ።

ፈሪ ሰው ካገኙ፣ ወያኔና ውሻ፣
አባረው መንከስ ነው፣ እስከመጨረሻ።

    የወያኔ ውሾች፣ ምንም ቢፎፎጡ፣
    ፊት አታሳዩዋቸው፣ አትደናገጡ፣
    እንደ ቆራጦቹ፣ እናንተም ቁረጡ።

ለተናካሽ ውሻ፣ ፍፁም መዲሃኒቱ፣
የጠዬ ሽመል ነው፣ ዋናው አብነቱ።

    እኛ እስከምናውቀው፣ በባህሉ መሰረት፣
    የሚናከስ ውሻ፣ አያበዛም ጩኸት፣
    ያ የእኛው ግቢ ግን፣ ህመሙ ጠንቶበት፣
    አቅሉን አጣ በቃ፣ አበደ ለየለት።

ተናካሹ ውሻ፣ ወያኔ ብኩኑ፣
ሲያዩት ይታወቃል፣ በከንፈሩ ባይኑ።

    የወያኔ ውሻ፣ ለተንኮል ሲፈልግ፣
    በከንፈሩም ባይኑም፣ ይታያል ሲያጨልግ።

ለተናካሽ ውሻ፣ ስግብግብ ወያኔ፣
የምግቡን አሰጣጥ፣ ዕወቀው ወገኔ።

    እየተነከሱ፣ እስከመቼ ማልቀስ?
    “ውሻ ከሚበላህ፣ በልተኸው ተቀደስ!”

ይኸ ዕብድ ውሻ፣ የተክለፈለፈ፣
ነክሶ ሳይጨርስህ፣ እየለካከፈ፣
ዕወቅ መዲሃኒቱን፣ ቀላል ነው ማርከሻው፣
እሾህ ለወጋው ሰው፣ እሾህ ነው መንቀሻው።

    ባጠገብህ ያለው፣ ሰረቀ፣ ደመቀ፣
    ዕብድ ውሻ ሲነክስህ፣ እያየ ከሳቀ፣
    እሱም ያው ዕብድ ነው፣ አወቀ፣ አላወቀ!

ወያኔ ዕብድ ውሻ፣ ጅራቱን ቆልፎ፣
ሳያጠፋህ አጥፋው፣ ለካክፎ አለካክፎ።

    ካበዱ ውሾች ጋር፣ አብረው የሚውሉ፣
    ካበዱ ውሾች ጋር፣ አብረው የሚበሉ፣
    ልክፍታሞች ናቸው፣ እነሱም በሙሉ፣
    ያልተለከፋችሁ፣ ቶሎ ገለል በሉ!

ስትመርጥ ተጠንቀቅ፣ ላሳስብህ እኔ፣
ያበደውን ውሻ፣ መርዘኛ ወያኔ፣
ወይንም የ’ሱን ግርፍ፣ የ’ሱን አሽከር ሎሌ፣
ወይም ጤነኛውን፣ ደፋር ባለወኔ፣
ምርጫው የራስህ ነው፣ ነቃ በል ወገኔ።